# የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፎች...የቀጠለ

በባለፈው ጽሁፍ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፎች መዋቅርን የተመለከትን ሲሆን በዚህ ጽሑፍ በህግ ማዕቀፎች የተካተቱ የተለያዩ ጉዳዮችን እንዳስሳለን።

## ስለግብይት አባልነት እና የምዝገባ ደንቦች

### የግብይትአባልነት መስፈርቶች

በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ እንደ የግብይት አባል መሳተፍ የተወሰኑ ህጋዊ እና የአሠራር መስፈርቶችን ለሚያሟሉ አካላት ብቻ የተወሰነ ነው። የግብይት አባል የሚሆን ማንኛውም አካል በካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ፈቃድ የተሰጠው ወይም ፈቃድ እንዲሰጠው በሂደት የሚገኝ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ወይም የአክሲዮን ማህበር መሆን አለበት።

የማመልከቻ ሂደቱ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀቶችን፣ የግብር መለያ ሰነዶችን፣ የኮርፖሬት መዋቅር መረጃዎችን እና የፋይናንስ መግለጫዎችን ማስገባትን ያካትታል። የግብይት አባል ለመሆን የሚፈልግ አመልካች ሙያዊ እና ቴክኒካዊ አቅም ያለው መሆኑን ማሳየት፣ የተገቢ ትምህርት ዝግጅት፣ ሥራ ልምድ እና ክህሎት መስፈርቶችን ማሟላት እና ለሠራተኞቻቸው የብቁነት እና ተገቢነት መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው።

አመልካቾች ከላይ የተገለጹ እና ሌሎች በገበያው ደንብ ውስጥ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ተቀባይነት ያገኙ አመልካቾች ለስድስት ወራት የሚፀና በመርህ ደረጃ የጸደቀ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል። በነዚህ ስድስት ወራት ውስጥ ከማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት የምዝገባ ማረጋገጫ እና ከአደጋ አስተዳደር እና የደንበኛህን-እወቅ ጋር የሚጣጣም አሰራር መዘርጋትን ጨምሮ ሌሎችንም መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። ገበያው የቅድመ ማረጋገጫ ፍተሻ ካደረገ በኋላ ሁሉም መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ከመርህ ደረጃ ማጽደቅ ወደ ሙሉ የግብይት አባልነት በማሳደግ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል።

## ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎችን በገበያው የመመዝገብ መስፈርቶች

የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የምዝገባ ደንብ (የደንቡ ጥራዝ ሐ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻቸውን ለማስመዝገብ የሚፈልጉ ኩባንያዎች መስፈርቶችን ያስቀምጣሉ። እነዚህም ግልጽነትን፣ ተገዢነትን እና የአሠራር እና የገለፃ ደረጃዎችን ማክበርን ያጎላሉ። አውጪዎች ለምዝገባው "ትክክለኛ እና ግልጽ መረጃ" ማቅረብ አለባቸው።

የሰነደ ሙዓለ ንዋይገበያ ማመልከቻዎችን በማጽደቅ ወይም ውድቅ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ውሳኔ ይሰጣል። ሁሉም የምዝገባ የቴክኒክ መስፈርቶች ቢሟሉም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጭው ለሕዝብ ጥቅም የማይሠራ እና ምክንያቶቹን የማይገልጽ ከሆነ ገበያው ማመልከቻውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል።

## የአዳጊ ገበያ ቦርድ - የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች መዳረሻ

የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ማዕቀፍ ልዩ ገጽታ በተለይ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተመዝግበው የሚገበያዩበት የአዳጊ ገበያ ቦርድ ያለው መሆኑ ነው። የዋናው ገበያ ቦርድ ለትላልቅ እና አቅም ላላቸው ኮርፖሬሽኖች አክሲዮኖች ምዝገባ እና ግብይት ተገቢ የሆኑ ጥብቅ መስፈርቶችን ያስቀምጣል። በአንፃሩ በአዳጊ ገበያ ቦርድ ላይ አክሲዮኖቻቸውን ለግብይት የሚያቀርቡ ኮርፖሬሽኖች መስፈርቶቻቸው በዋናነት ለግብይት የቀረበው አክሲዮን መጠን ዝቅተኛ መሆን እና ብዙም ያልተጋነነ የፋይናንስ አቅም ያሏቸው መሆኑ ነው።

ይህ አወቃቀር በማደግ ላይ ባለ ገበያውስጥ ሊያጋጥም የሚችለውን መሠረታዊ ፈተና የሚፈታ ነው። ይህም ከፍተኛ የምዝገባ ደረጃዎችን የሚያስቀምጠውን ዋና ቦርድ ከኢንቨስተሮች ጥበቃ መርህ አንጻር እንዲሁም ለአነስተኛ አውጪዎች ተደራሽ መንገዶችን የሚፈልገውን አዳጊ ቦርድ ከገበያ ልማት መርህ አንፃር የሚያመጣጥን ነው።

## የምዝገባ ክፍያዎች

በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ለሚደረግ ምዝገባ ክፍያ ከገበያው መተዳደሪያ ደንብ ጋር በተያያዘው የክፍያ መርሃ ግብር ውስጥ ተዘርዝሮ ይገኛል። ይሁን እንጂ ገበያው እንደየነገሩ ሁኔታ የሚቀርቡ ጉዳዮችን አንድ በአንድ እያየ ክፍያዎችን የመተው መብቱ የተጠበቀ ነው። ይህ ውሳኔ ገበያው ደንቡን ማሻሻል ሳያስፈልገው እንደ ፕራይቬታይዜሽን እየተደረገ ያሉ የመንግስት ባለቤትነት ያላቸው ድርጅቶች ወደ ግል የማዞር ወይም ስትራቴጂካዊ የግል ዘርፍ ያሉ ተፈላጊ ድርጅቶችን ምዝገባ ከክፍያ ነጻ በማድረግ ሥርዓቱን ማበረታታት ያስችለዋል።

## የኢንቨስተር ጥበቃ - የህግ ጥበቃዎች የተከለከሉ የግብይት ተግባራት

የህግ ማዕቀፉ የገበያ ተዓማኒነትን የሚያዳክም ወይም የሚሸረሸር ምግባርን በግልጽ ይከለክላል። ይህም የገበያ ማጭበርበርን፣ አርቲፊሻል በሆነ መልኩ የሰነዶች ዋጋዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር፣ የውስጥ አዋቂ ግብይት መፈጸም እና የውሸት የመረጃ ስርጭትን ያካትታል። እነዚህ ክልከላዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ህጎች ውስጥ መደበኛ ናቸው፣ ይህም የኢንቨስተር በራስ መተማመን በገበያው ታዓማኒነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እውቅና ይሰጣል።



የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

## ወሳኝ ወይም ቁሳዊ መረጃዎችን ይፋ ስለማድረግ

በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ ውስጥ ያለው ዋና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴ የአውጪው ወሳኝ መረጃዎችን የግዴታ ይፋ ማድረግ ነው። ይህ ወሳኝ መረጃዎችን በአውጪው ይፋ የማድረግ ንድፈ ሐሳብ ከዘመናዊ የሰነድ ሙዓለ ንዋዮች የቁጥጥር ሕጎች ጋር የሚስማማና ኢንቨስተሩ ሰለሚገዛው ድርጅት አክሲዮን በቂ መረጃ ኖሮት እንዲወስን ያስችለዋል።ይህ አካሄድ በተለይ የፋይናንስ እውቀት ውስን በሆነባት ሀገር ውስጥ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

በዚህ ረገድ ተቆጣጣሪ አካላት አንድን አክሲዮን ለሕዝብ ለመሸጥ ያወጣ አውጪ ኩባንያ ሁኔታ "በጣም አደገኛ" በሚል የአክሲዮን ሽያጭን ከመከልከል ይልቅ አውጪው ይፋ በማድረግ ግዴታው መሰረት በየጊዜው የሚያወጣቸውን መረጃዎች ትክክለኛ፣ ወቅታዊ እና ተደራሽ መሆኑን ማረጋገጥ ላይ ማተኮር ይገባቸዋል።

## ለኢንቨስተሮች - መፍትሄዎች

የካፒታል ገበያ የሕግማዕቀፍ ጥሰቶች በሚከሰቱበት ጊዜ ጉዳት ለደረሰባቸውኢንቨስተሮች መፍትሄዎችን የሚሰጥ ነው። የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ የክርክር አፈታት ሂደቶችን የሚያካትት ሆኖ ከካሳ ፈንድ ካሳ የሚከፈልበትንም ሥርዓት የዘረጋ ነው። በዚህ ሂደት የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ጥሰቶችን የመመርመር እና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመውሰድ፣ ቅጣቶችን የመጣል፣ ፈቃዶችን የማገድ እና ሌሎች መሰል እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን ተሰጥቶታል።

## የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ

ከሕዝብ እና ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር የተደረገበት የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ረቂቅ መመሪያ የኢንቨስተሮች ጥበቃ፣ የተደራሽነት ስልቶችን እና የኢንቨስትመንት አማራጮችን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያሰፋፋ ነው። በካፒታል ገበያ አዋጅ እንደተመለከተው የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ማለት ሰዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም ሌሎች ንብረቶችን በባለቤትነት በመያዝ፣ በይዞታ በማቆየት፣ በማስተዳደር፣ ወይም በማስተላለፍ ገቢ ወይም ትርፍ ለማግኘት የሚሳተፉበት ወይም ይህን ዓይነት ዓላማ ወይም ውጤት ለማስገኘት ታስቦ የተቋቋመ ወይም ከእንደዚህ ዓይነት አሰራር ከሚገኝ ገቢ ወይም ትርፍ የሚከፈልበት የስምምነት መዋቅር ነው።

በስምምነት መዋቅሩ ውስጥ ገንዘብ የሚያዋጡ ኢንቨስተሮች በፈንዱ የእለት ተዕለት ሥራ እና ቁጥጥር የማይሳተፉ ሲሆን ይህ ስራ የሚመራው ለዚሁ አላማ ተብሎ ከካፒታል ገበያ ባለስልጣን የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ለማስተዳደር የአከናዋኝነት ፈቃድ በተሰጠው ድርጅት ነው። የፈንዱ አከናዋኝ ወይም በሌሎች ሃገራት ፈንድ አስተዳዳሪ እየተባለ የሚጠራው ከተለያዩ ኢንቨስተሮች ገንዘብ እየሰበሰበ በምትኩ በሰበሰበው ገንዘብ ልክ የባለድርሻነት ድርሻ ክፍልፋዮችን እየሰጣቸው ገንዘባቸውን በባለስልጣኑ እንዳስመዘገበበት እና ፈቃድ እንዳገኘበት የፈንድ አይነት በአክሲዮኖች፣ቦንዶች፣ የአጭር ጊዜ የግምጃ ቤት ሰነዶች፣ የሪል ስቴት ኢንቨስትመንቶች እየገዛላቸው እና ከመልሶ ሽያጭ፣ ከኪራይ እና ሌሎች ምንጮች የሚገኘውን ገቢ በዲቪዴንድ ወይም በትርፍ መልክ ለአባላቱ የሚከፍልበት ሥርዓት ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ለዚህ ፈንድ ገንዘብ ያዋጡ ኢንቨስተሮች በፈንዱ ባላቸው የባለቤትነት ድርሻ ክፍልፋዮች ልክ ከፈንዱ ትርፍ ብቻ ሳይሆን ከኪሳራ እና ወጪዎችም እንደሚጋሩ ነው።

ይህ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥርዓት የፈንዱ አከናዋኝ የፈንዱን ሀብት እና የአባላቱን ሂሳቦች በኃላፊነት የሚያስተዳድርበት የኢንቨስትመንት መሳሪያ ነው። ረቂቅ መመሪያው የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶችን ለመመዝገብ፣ ለማከናወን እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ የሚያበጅ ሲሆን የቁጥጥር እና አሰራር ደንቦች እና ሁኔታዎችን አካቷል።

የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ የምዝገባ ሂደት በፈንዱ አከናዋኝ የሚመራ ሲሆን ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ባለው የኢንቨስትመንት አማካሪ በኩል የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በማዘጋጀት እና ለባለሥልጣኑ ለምዝገባ በማቅረብ ይከናወናል። የደንበኛ ሳቢ መግለጫው እንዲመዘገብ የታለመውን የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስም፣ አድራሻ፣ የታቀደ የካፒታል ጣሪያ፣ የፈንዱ የባለቤትነት ድርሻ ክፍልፋዮች አይነት፣ የክፍፍል ፖሊሲ፣ ትርፍ እና ወለድ የሚከፈሉበትን ቀናት እና የግብር አያያዝን ጨምሮ መሰረታዊ መረጃዎችን ያካተተ መሆን አለበት። የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች የተለያዩ የኢንቨስትመንት መሳሪያዎችን በማቅረብ እና ሙያዊ የአስተዳደር አገልግሎትን በመስጠት ለመደበኛ ኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

## እድሎች-የለውጥ አቅም

የካፒታል ገበያን ዘግይቶ በመጀመር እንደሃገር የቀረብን ጥቅም ቢኖርም አጋጣሚውን ወደ መልካም በመቀየር ልንጠቀምበት እንችላለን። ለምሳሌ ተመሳሳይ ሽግግሮችን ካስተናገዱ የአቻ አገራት ምርጥ ተሞክሮዎች እና ልምዶችን መቅሰም እንችላለን። በዚህ ረገድ ቴክኖሎጂ ለትምህርት እና የእውቀት ሽግግር ማዕከላዊ ሆኖ ያገለግላል። ግዑዝ አልባ በተደረጉ እና በኤሌክትሮኒክስ መልክ በተያዙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚደረግ የዲጂታል ግብይት የማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት ስርዓቶች እና የእውነተኛ ጊዜ የገበያ ክትትል በካፒታል ገበያ የሚደረገውን ተሳትፎን ለማስፋት እና የፋይናንስ ማካተትን ለመደገፍ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

ሌላው እድል በተለያዩ ሀገራት የሚኖረው ትልቅ የዲያስፖራ ማህበረሰብ ከፍተኛ የካፒታል ገበያ ኢንቨስትመንት ምንጭ የመሆን አቅም ያለው ነው። ግልጽ የሆነ የህዝብ ግንኙነት፣ የኢንቨስተሮች ተደራሽነት እና ከዲያስፖራ ማህበረሰቦች ጋር ያለው ተሳትፎ እምነትን እና አካታችነትን ለማሳደግ የሚረዱ ናቸው። የካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፍ ለውጭ ኢንቨስትመንት ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች ቅርብ ጊዜ ከተደረገው የውጪ ምንዛሪ በገበያ የመወሰን እና የውጪ ምንዛሪ ሂሳብ መያዝ እና "ያለገደብ" የማንቀሳቀስ አካሄድ ተዳምሮ ቀደም ሲል ያልነበሩ የዲያስፖራ ካፒታል ገበያ አሳታፊነት መንገዶችን ፈጥሯል።

## የአፍሪካ የካፒታል ገበያዎች ቅንጅት ተስፋ

ከካፒታል ገበያ ጋር በተያያዘ ከሌሎች ሀገራት ጋር አህጉራዊ ቅንጅት እና ውህደት ራዕይ ማድረግ ተገቢ ነው። ከሌሎች አህጉራት አንፃር በካፒታል ገበያ የአፍሪካ የነፍስ ወከፍ ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ ነው። በዚህ ረገድ የሀገራት የካፒታል ገበያ ቅንጅት እና ውህደት የአፍሪካን የፋይናንስ ገደቦች የመፍታት አቅም አለው። በዚህ ቅንጅት እና ውህደት የሚፈጠር የፓን አፍሪካ የካፒታል ገበያ የተለያዩ የኢንቨስትመንት መሳሪያዎችን፣ ቀልጣፋ መሠረተ ልማትን፣ የገበያ ጥልቀትን እና ቶሎ የመሸጥ እና የመግዛት ሁኔታን ይፈጥራል። ይህ ስትራቴጂካዊ አተያይ ሀገሪቱን በአህጉር የገበያ ትስስር ውስጥ እንድትሳተፍ የሚረዳ ነው።

## በፈጠራበኩል የሚደረግ የፋይናንስአካታችነት

የካፒታል ገበያ የሕግማዕቀፍ ባህላዊው የባንክ ተኮር ስርዓቶች ሊዛመዱ እና ሊያስተናግዱ የማይችሉትን የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶችን፣ የሸሪዓ ህግን የተከተሉ የካፒታል ገበያ መሳሪያዎችን እና የዲጂታል የግብይት መድረኮችን ማስተናገድ የሚያስችለውን ሥርዓት እና የፋይናንስ አካታችነት እድሎችን ፈጥሯል። በመሆኑም ሁሉን አቀፍ የፋይናንስ አሰራር መዘርጋት ለጋራ ብልጽግና ወሳኝ መሆኑን፣ የካፒታል ገበያ ልማት በራሱ እንደ መጨረሻ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ተሳትፎን ለማስፋት እንደ መንገድ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑን ልብ ይሏል።



የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት